በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስቅዱስ

አሐዱ አምላክ አሜን፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፺

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:-** kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf : www.zeorthodox.org

***ቦታ፡-*** ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

ኅዳር ፬ ቀን ፳፻፮ ዓ.ም.

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፯

- ነህምያ ናቡከደነፆር ኢየሩሳሌምን ካፈራረሳት በኋላ የከተማይቱን ቅጥሮች መልሶ ለመሥራት ታላቅ ኃላፊነት የተቀበለ ሰው ነበር፡፡ ይህን ታላቅ ሥራና ኃላፊነትም የሰጠው እግዚአብሔር ነበር፡፡
- ነህምያ ያሰራው ቅጥርም ደኅንነታቸውን፣ ክብራቸውን... የሚወክልላቸው ሲሆን ሠርቶ መፈጸምም የሚያስችል ከፍተኛ አመራርና መነሳሳት ይፈልግ ነበር፡፡ ነህምያ እስካሁን ሁሉን ተቋቁሞ እየሠራ ነው፡፡
- ዛሬ የምንመለከተው የቅጥሩን ሥራ ሲሰራ ስለደረሰበት ማስፈራሪያና ዛቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሊጠቀምብን ከመረጠን ማስፈራሪያና ዛቻ የሚገጥመን መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡
- ታዲያ ዛቻ ወይም ማስፈራሪያ ሲገጥመን ምን ማድረግ ይኖርብናል? ማድረግ ያለብንን የምንማረው ከመጽሐፈ ነህምያ ምዕራፍ ስድስት ነው፡፡ በቅድሚያ ግን መሪዎች በተቃውሞ፣ በጠብና በክርክር የተነሣ የሥራ ጊዜያቸው ሳይቀር እንደሚወሰድባቸውና ይህም በዓለም የተለመደ መሆኑን እናስተውል፡፡
- አንድ ተልዕኮ ለመፈጸም ስንዘጋጅ የአቅማችንን (የጉልበታችንን) ሁለት ሦስተኛ (ስድሳ ሰባት ፐርሰንት) የሚገጥሙንን ተቃውሞዎችና አስቸጋሪ የሆኑ ሁኔታዎችን ለመዋጋት እንደምናጠፋው እናውቃለን? ተቃውሞዎቹና አስቸጋሪ ሁኔታዎቹም ከውስጥ የሚመነጩ ወይም ከውጪ የሚመጡ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ይህም የሚያረጋግጥልን ከሥራ ጊዜያችን ባለን አቅም ሁሉ በአግባቡ የምንጠቀመው አንድ ሦስተኛውን (ሠላሳ ሦስት ፐርሰንቱን) ያህል ብቻ እንደሆነ ነው፡፡
- በርካታ ሰዎች ሁለት ሦስተኛ (ስድሳ ሰባት ፐርሰንት) ጉልበቴን ለዚህ መሰል ጉዳይ ስለምን አጠፋለሁ ይላሉ፡፡ አንድ አገልግሎትም ይጀምሩና ሁለት ሦስተኛ (ስድሳ ሰባት ፐርሰንት) ተቃውሞ፣ እንቅፋት ወዘተ ሲገጥማቸው ለምን ይህ ሁሉ ስለምን ይሆናል? ለምሰጠውስ አገልግሎት ተመጣጣኝ ነውን? አይደለም፤ ስለዚህም ከዚህ መሰል ጉዳይ ጋር ምን አታገለኝ ብለው ይተውታል፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፯

- እንግዲህ ከሁሉ በላይ ይህ አቅጣጫ አመራር እንደሆነ እናስተውል፤ እኛም እንደ ክርስቲያን የመሪነት ድርሻችንን መወጣት ይጠበቅብናል፡፡ እንኳን ለአመራር ሰጪነት አበቃችሁ አበቃን! አሜን፡፡
- መጽሐፈ ነህምያን ስናነበው በብዛት ስለ ድንጋይ፣ ስለ ድንጋይ መጥረቢያዎች፣ ስለ ድማሚት፣ ስለ ሲሚንቶ... አይናገርም፡፡ ይልቁኑ ስለችግሮችና ስለ ገጠሙት ተቃውሞዎች ያነሳና እነዚህን ችግሮች እንዴት እንደተወጣቸው ያስረዳናል፡፡
- እኛም የእግዚአብሔርን ለመሥራት ተነስተን ሥራውን ያለ ተቃውሞና ያለ ነቀፋ ለመፈጸም አስበን እንደሆነ ምን እንደምንሠራ፣ ለማን እንደምንሠራና ምን እንደምናገርም አናውቅም ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ለርሱ በምንሠራው ሥራም ሆነ በምንሰጠው አገልግሎት ተቃውሞ እንዲገጥመን ከመፍቀድ ጋር ተቃውሞውን በመጠቀም ሥራውን የተከናወነ ያደርግልናል፡፡
- እግዚአብሔር ከአገልግሎት ይልቅ ለአገልጋዩ፣ ከሥራው ወይም ከፕሮጀክቱ ይልቅ ለመሪው የበለጠ ይጠነቀቃል፡፡ ይህንም ለማስረዳት ብዙ መድከምም አያሻንም፤ ብዙ ምስክሮች በመጻሕፍት አሉልንና!!!
- አንዳንድ ሰዎች ታማኝና መልካም ሆነው ሳሉ በርካታ ችግሮችን የሚጋፈጡት እግዚአብሔር በችግሩ ውስጥ ጽናታቸውን፣ ምግባራቸውን፣ ጠባያቸውን ቅርጽ ስለሚያስይዝና መልካምነትን ስለሚያስተምር ነው፡
- ከነዚህም ጋር ቅዱስ ያዕቆብ ‹‹ወንድሞቼ ሆይ፥ የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ፥ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቍጠሩት፡፡ ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም፡፡›› ***ያዕ 1፥2-4፡፡*** በማለት እንደጻፈው ፍጹም ሰው ወደ መሆን የምታደርሰውን ትዕግሥትን ይቀርጽባቸዋል፡፡ መሪ መሆን ከፈለግን በተቃውሞ ውስጥ ማለፍን በማወቅ ከመመላለስ ጋር እነዚህ ሁሉ እንማር እንጂ ወደ ኋላ አንመለስ፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፯

- ከዛሬው ትምህርታችን በፊት ስለ እቅድ፣ ስለ ነቀፋና ተስፋ ስለሚያስቆርጡ ፈተናዎች ተምረናል፤ ዛሬ ደግሞ ስለ ዛቻና ማስፈራሪያ እነዚህንም ተቋቁሞ ሥራንና አገልግሎትን ስለማከናወን እንማራለን፡፡
- ‹‹እንዲህም ሆነ ቅጥሩን እንደ ሠራሁ፥ ከፍራሹም አንዳች እንዳልቀረበት ሰንባላጥና ጦብያ ዓረባዊውም ጌሳም የቀሩትም ጠላቶቻችን ሰሙ ነገር ግን እስከዚያ ጊዜ ድረስ በበሮቹ ውስጥ ሳንቃዎቹን አላቆምሁም ነበር።›› ***ነህ 6፥1፡፡***
- እነዚህ ሦስቱ ጠላቶቹ ወይም ተቃዋሚዎቹ (እንዳልቀረበት ሰንባላጥና ጦብያ ዓረባዊውም ጌሳም) እጅ አልሰጡም፤ ደጋግመው ይመጡና ይፈትኑት ነበር፡፡
- ‹‹ተመልከቱ ሰውየው ቀላል አይደለም፣ ሥራውን እየሠራ ነው፣ ቅጥሩን ፈጽሞታል፣ የቀረው በሮቹን መግጠም ነው፤ ብቃወመውም ሥራውን አላቆመም…›› ተባባሉ፡፡
- ከባዱ ፈተናና የሚያስከትለውም የከፋ ጉዳት የሚገጥመን ወደ ድል ስንቃረብና ድልም ስናደርግ ነው፡፡ ‹‹ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመስለው እንዳይወድቅ ይጠንቀቅ።›› ***ቀዳ ቆሮ 10፥12፡፡***
- ለውድቀት የምንጋለጠው በሁለት እግራችን መቆም ችለናል በምንልበት ጊዜ ነው፡፡
- ንጉሥ ዳዊት የወደቀው ጠላቶቹ ሲዋጉትና በጦር አደባባይ በነበረበት ጊዜ አልነበረም፡፡ ድል ካደረገ፣ ጠላቶቹን ከጣለ ካሻነፈ በኋላ በእረፍት ላይ ሳለ ከቤርሳቤህ ጋር ወደቀ፡፡ ቆሜያለሁ ብሎ ሲያስብ በከፍታው ጊዜ ወደቀ፡፡ ***ካል ሳሙ 12፡፡***
- ዮናስ ራስን በመውደድ ፈተና የወደቀው የነነዌን ሰዎች ሁሉ ለንስሐ ካበቃ በኋላ ነበር፡፡ ***ዮና 4፡፡***
- ኤልያስም በአክዓብና በኤልዛቤል ላይ ታላቅ ድል ከተቀዳጀ በኋላ ተስፋ በመቁረጥ ተገኘ፡፡ ***ቀዳ ነገ 19፡፡***
- ዮሴፍም በቤተ መንግሥቱ ከፍታን ባገኘና በገነነ ጊዜ ተፈተነ፡፡
- ቆሜያለሁ ብለን ስናስብ ከማንኛውም ጊዜ ይልቅ ለውድቀት የተጋለጥን መሆናችንን እናስተውል፡፡

# <u>መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፯</u>

- ይህም ለማንኛውም ሰው የሚደረግ ነው፡፡ እግዚአብሔር በሕይወታችን ታላላቅ ነገሮችን ሲያደርግልን እጅግ እንፈተናለን፣ ለመሰናክሎችም የተጋለጥን እንሆናለን፡፡
- ነህምያም ሁሉን አከናውኖ በሮቹንም ለመግጠም ሲዳረስ በሦስት መንገዶች ተፈተነ፡፡
- በዚህም የምናየው የእግዚአብሔር ዓላማው በችግሮቹ እኛን ማላላት ማዳከም ሳይሆን የበለጠ ማበርታት ነው፡፡ አንድ ሰው ስንወድ ያ ሰው ደስተኛ እንዲሆን እንፈልጋለን፤ እግዚአብሔር ግን ቅዱስ እዲሆን ይሻል፡፡ ይህም ታላቅ ልዩነት ነው፡፡ ደስተኛ እንዲሆን ሳይሆን ቅዱስ እንዲሆን ይሻል፡፡
- እኛ በየቀኑ የምንፈልገው ደስ መሰኘት፣ ከሕመማችን እንዲሻለን፣ ወዘተ እንሻለን ይህንም አንዳንድ ጊዜ ግብ እናደርገዋለን፤ የእግዚአብሔር ዓላማው ግን ቅዱሳን እንሆን ዘንድ ነው፡፡
- ነህምያ ከፊት ይልቅ እጅግ ይበረታ ዘንድ በሦስት መንገዶች ተፈተነ፡፡

1. ***<u>የግል ግብዣ አደረጉለት፡፡</u>*** ‹‹ሰንባላጥና ጌሳም፡ መጥተህ በኦኖ ቈላ ውስጥ ባሉት መንደሮች እንገናኝ ብለው ላኩብኝ ነገር ግን ክፉ ያደርጉብኝ ዘንድ ያስቡ ነበር።›› ***<u>ነህ 6፡2፡፡</u>***

- ሥራህን ሠርተሃልና አሁን እንገናኝ አሉት፡፡ ሰዎቹም ‹‹የሆነው ሆኖአል፣ ምርጫው ተጠናቋል አሸንፈሃል፣ አሁን ወዳጆች እንሁን›› ያሉ ዓይነት ይመስላል፡፡ ነህምያ ግን ክፉ ያደርጉብኝ ዘንድ ያስቡ ነበር በማለት አይሆንም፣ አልመጣም አላቸው፡፡ ነህምያ ብልህና አስተዋይ ይመስላችኋል?
- ትንሽ ወጣ ያለ ማንነት አይመስልም? ቅጥር እየሠራ ነው፣ እነርሱ ጠላቶቹ ናቸው ሄዶ ማናገርና ማሳመን አይገባውምን? ኦኖ በአበቦችና በተለያዩ ተክሎች ያጌጠች ከኢየሩሳሌም በስተ ሰሜን 35 ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ የምትገኝ እንደ ሪሶርት ያለች ሥፍራ ናት፡፡ ‹‹በሥራ ደክመሃል ስለምን መጥተህ አትዝናናም? እስኪ መጥተህ በባህር ዳርቻ (Beach) እንገናኝ›› አሉት፡፡ ነህምያም አይሆንም፣ አልመጣም አለ፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፯

- ለምን? ቅዱስ እንጦንስ በአንድ ወቅት ‹‹ከመልካም ሥራዎች ሁሉ የምትልቀው ምንድን ናት? ብሎ ጠየቀ፡፡ ፍቅር ብለው መለሱለት፤ አይደለም አላቸው፡፡ እንግዲያውስ ትሕትና ናት አሉት፤ አይደለችም አለ፡፡ በመጨረሻም ክፉንና በጎን ለይቶ ማወቅና ቁርጠኝነት ናት፡፡›› ብሎ መለሰላቸው፡፡
- ፍቅር በቂ አይደለም፤ ከፍቅርም የሚጎዳ ፍቅር አለና፡፡ አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸውን እስኪበላሹ - እስኪጠፉ ድረስ የሚወዱበት ፍቅር ጎጂ ፍቅር ነው፡፡ ዓለምን መውደድም እንዲሁ የምትጎዳ ናት፡፡
- ክፉንና በጎን መለየትና ቁርጠኝነት መውደድ ብቻ ሳትሆን እንዴት መውደድ እንዳለብን ማወቅም ናት፡፡
- መቼ ትሑት፣ ንቁ፣ አቋም መያዝ እንዳለብን ማወቅ ታላቅ ሀብት ነው፡፡
- ነህምያ ሰዎቹ ተቃዋሚዎችና ጠላቶች ሆነው ሳሉ እንገናኝ ብለው ቢጠይቁት አይሆንም አላቸው፡፡ ለምን?
- ‹‹እኔም። ትልቅ ሥራ እሠራለሁ፥ እወርድም ዘንድ አይቻለኝም ሥራውን ትቼ ወደ እናንተ በመውረዴ ስለ ምን ሥራው ይታጐላል? ብዬ መልእክተኞችን ላክሁባቸው።›› ***ነህ 6፥3፡፡*** አለ፡፡
- ይህ አነጋገር አሁንም ንቀት ያለበት አይመስልም፡፡ ነህምያ ከትሕትናውና ከፍቅሩ ጋር ክፉና በጎን ለይቶ የሚያውቅበት ጥበብ ነበረው፡፡ ከዚህ የሚሻልም ምላሽ ሊሰጣቸው አይችልምና ‹‹ትልቅ ሥራ እሠራለሁ እወርድም ዘንድ አይቻለኝም›› ብሎ መለሰላቸው፡፡
- ለምሳሌ እኛ ክርስቲያኖች፣ አገልጋዮች፣... ነን ወደ አንድ አጠያያቂ ቦታ(ጭፈራ ቤት፣ ጠንቋይ ቤት፣ ...) እንድንገኝ ተጋበዝን እንበል፡፡ ውረዱ ተባልን - እንወርዳለን ወይስ አንወርድም?
- ነህምያ እግዚአብሔር ታላቅ ሥራ ሰጥቶኛል አለ እንጂ እኔ ታላቅ ሰው ነኝ አላለም፡፡ እግዚአብሔር ይህን ታላቅ ኃላፊነት ሰጥቶኝ ሳለ ወደ እናንተ ስለምን እወርዳለሁ? አላቸው፡፡
- ማንኛውም ክርስቲያንና አገልጋይ የምሠራው ታላቅ ሥራ አለኝና አልወርድም ማለት ይኖርበታል፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፯

- እግዚአብሔር ታላቅ ሥራ ሰጥቶኝ ሳለ ሁለት ሰዓት ሙሉ ስለምን ፊልም አያለሁ... ማለት ይጠበቅብናል፡፡
- ታላቅ ሥራ እየሠራሁ ነው ሥራውም ከእግዚአብሔር ነው አለ እንጂ እኔ ታላቅ ነኝ፣ ከእናንተ እሻላለሁ ሲል አልተገኘም፡፡ ይህም የሚቀድመውንና የሚከተለውን ለይቶ የማወቅ ችሎታ ነው፡፡
- የሚቀድመውንና የሚከተለውን ለይተው ማወቅ የማይችሉ ሰዎች ፈጽመው መሪም ሆነ ስኬታማ ሰው መሆን አይችሉም፡፡ ይህንም ማወቅ አልችልም፣ አይሆንም ... ወዘተ ለማለት በመቻል ይገለጻል፡፡
- አንዳንድ ጊዜ መሪዎችና ተራ ሰዎች የሚለያዩት አልችልም፣ አይሆንም... ማለት በመቻልና ባለመቻል ነው፡፡ እኛስ ይህን ማለት እንችላለን? መልካም ነገርን አይሆንም ማለት እንችላለን? አዎ የሚበልጠውን ለማድረግ ስንል አይሆንም ልንል እንችላለን፡፡ ወደ ጉባኤ እየሄድን ነው እንሂድ ሲሉን አዎ መሄድ እፈልጋለሁ ነገር ግን የምሠራው ነገር አለን ማለት መቻል የመሪ መለያው ነው፤ የሚልቀውን ለመሥራት
- መሪ የምንለው ለከፉ ነገር እሺ የሚለውን አይደለም፤ የሚልቀውን ለማድረግ እምቢ የሚለውን እንጂ፡፡
- ‹‹እንዲህም ቃል አራት ጊዜ ላኩብኝ እኔም እንደ ፊተኛው ቃል መለስሁላቸው።›› ***<u>ነህ 6፥4፡፡</u>***
- አራት ጊዜ ላኩበት፣ አይሆንም ሥራ ላይ ነኝ አላቸው፡፡

2. ***<u>ክፍት ደብዳቤ ላከለት፡፡</u>*** ‹‹ሰንባላጥም እንደ ፊተኛው ጊዜ ብላቴናውን አምስተኛ ጊዜ ላከብኝ ፡፡›› ***<u>ነህ 6፥5፡፡</u>*** አሁን በሁሉ ፊት የሚነበብ ደብዳቤ ላከለት፡፡ አስቀድሞ እንገናኝ የሚል ዓይነት አሁን አምስተኛውን መልእክት ግን ይኸ ሰው (ነህምያ) ሥርዓተ አልበኛ ነው ለማሰኘት ሰንባላጥ በሁሉ ዘንድ በሚነበብበት መልኩ ደብዳቤ ላከለት ፡፡

- የተላከው ክፍት ደብዳቤም ‹‹በእጁም ውስጥ። አንተና አይሁድ ዓመፅ እንድታስቡ፥ ስለዚህም ቅጥሩን እንድትሠራ፥ ንጉሣቸውም ትሆን ዘንድ እንድትወድድ በአሕዛብ ዘንድ ተሰምቶአል። ደግሞም፦ ንጉሥ በይሁዳ አለ ብለው ስለ አንተ በኢየሩሳሌም ይናገሩ ዘንድ ነቢያትን አቁመሃል አሁንም ለንጉሡ ይህን ቃል ያወሩለታል እንግዲህ መጥተህ በአንድነት እንማከር የሚል ክፍት ደብዳቤ ነበረ።›› ***<u>ነህ 6፥6-7፡፡</u>***

# <u>መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፯</u>

- የመጀመሪያው አመጣጣቸው እንገኛኝ ዓይነት ነበር፤ ሁለተኛው ግን ያልሆነውን ሆነ ብሎ የማስወራት (ስም የማጥፋት) ዘመቻ ነበር፡፡
- ከፋርሱ ንጉሥ ከአርጤምሲስ ጋር ለማጋጨት ፈልገው አንተና አይሁድ በንጉሡ ታምጻላችሁ፣ አንተም ንጉሥ መሆን እንደምትወድ ይህንም ይናገሩልህ ዘንድ ነቢያትን እንዳደረግህ አውቀናል አሉት፡፡ ነህምያ መሪ ወይም ገዢ እንጂ ንጉሥ አልነበረም፡፡
- ያልሆነውን ሆነ ብሎ ማስወራት (ስም ማጥፋት) ማለት ምንድን ነው? አንደኛ ምንጭ የለውም - ሰማሁ፣ ሰዎች ይላሉ፣ እነርሱ አሉ ብቻ በማለት መጮህ ሲሆን ሁለተኛው የተጋነነና ያልተረጋገጠ መሆኑ ነው፡፡
- እነዚህ ሰዎች የሚናገሩት ፍጹም ያልተደረገ ያልሆነ ነገር ነበር፤ ታዲያ ይህ አይጎዳም? ይጎዳል እንጂ፡፡
- ከሰው ጋር ተስማምቶ/ተስማምታ የማይሰራ/የማትሰራ ነው/ናት፣ ታማኝ አይደለም/ችም... ተብለን ስማችን ቢነሳ ይልቁኑ የተወራው መቶ ፐርሰንት ሐሰት ቢሆን የሚሰማን ምንድነው? አይጎዳንም አያመንም? ይጎዳል ያማል፡፡
- ይልቁኑ የተወራብን ከማንነታችንንና ከምግባራችን ጋር የሚጋጭ ከሆነ የመሞት - የመገደል ያህል ነው፡፡
- ታዲያ ይህ ሁሉ ሲወራ ነህምያ ሄደ ወይስ አልሄደም? ካልሄደ ወሬው እየሰፋ ይሄዳል፡፡ ከሄደ ደግሞ ሥራውን በማበላሸት ለጠላቶቹ የድል ቀንና ሁኔታን ያመቻችላቸዋል፡፡ ያደረገውን እንመልከት፡፡
- የቤተሰብ፣ የማኅበረሰብ፣ የምዕመናንም ሆነ የአገር "ቁጥር አንድ ገዳይ" ነገር ያልሆነውን ሆነ ብሎ የማስወራት (ስም የማጥፋት) ዘመቻ ነው፡፡
- በቤተ ክርስቲያን ያሉ ሰዎች ይልቁኑ በውስጥ ያሉት ከሌሎች ይልቅ ያልሆነውን ሆነ ብሎ በማስወራት (ስም የማጥፋት) ዘመቻ ከሌሎች ይልቅ ተጠቂ እንደሆኑ እናውቃለን? ***<u>ዮሐ 20፡፡</u>***
- ያወቁበትና የነቁበት ባሉበት ስለዚህና ስለዚያ እያሉ የምሕላ ጸሎት ሳይቀር ያደርሳሉ፡፡

# <u>መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፯</u>

- ሌሎቹ ደግሞ ስለ እያንዳንዱን አገልግሎት እየናቁና እየሰነጠቁ ያወራሉ፣ ይነቅፋሉ፣ ... ይህም የክርስቶስ አካል የሆነች ቤተ ክርስቲያንንና ምዕመናንን ያጠፋል፡፡ ***<u>ኤፌ 1፥20-23</u>*** ካነበብብ በኋላ... ‹‹ለሚሰሙት ጸጋን ይሰጥ ዘንድ፥ እንደሚያስፈልግ ***<u>ለማነጽ የሚጠቅም ማናቸውም በጎ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ።</u>***›› ***<u>ኤፌ 4፥29፡፡</u>*** በማለት ለማነጽ የሚጠቅመውን በጎ ቃል ብቻ እንዲጠቀሙ ይመክራል፡፡
- አሁንም የምለምናችሁ ***<u>ቢያዕ 3፥6</u>*** የተገለጸውን እሳት የሆነ አንደበታችንን ከመክፈታችሁ በፊት የምትናገሩትን እንድታስቡ እመክራችኋለሁ፡፡ ከሁሉ አስቀድመን የምንናገረው ሰውን ይጠቅማል፣ የታወቀና እውነተኛ ምንጭ አለው፣ ወይም ዝም ብዬ ሰምቼ ነው የማወራው ብለን ራሳችንን እንመርምር፡፡
- በማንኛውም መንገድ ሰውን የማይጠቅም፣ የማያንጽም ነገር ከመናገር እንቆጠብ፡፡ ካልተቆጠብን ሰውን፣ ማኅበረሰቡን፣ ባልንጀሮቻችንን እናጠፋቸዋለን - ሰማሁ - ብለን ሰማሁ እያሉ እንዲያጠፉ እንጋብዛለንና፡፡
- እነርሱ ይህ ሲባል ሰምተናል አሉ፡፡ ታዲያ ይህን የምንቋቋምበት ግልጽ መንገድ የቱ ይሆን? ፊት ለፊት መጋፈጥ ነው፡፡ ስለምትናገረው ነገር እርግጠኛ ነህ? ካልሆንክ ደግመህ አትናገረው፤ ሰውን ያሳስታልና በማለት መጋፈጥ የተሻለ መንገድ ነው፡፡ እኛ ስለ እውነት መከራከር እንችላለን?
- ለምሳሌ ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ውስጥ ቦምብ የሚጥል ሰው አይተን እንዳላየ እንዳልሰማ ዝም ብንል ምን የምንላችሁ ይመስላችኋል? በወንጀሉ ተባባሪ ናችሁ ብለን እንጠይቃችኋለን፡፡ ያለሆነውን ሆኗል ብለን ማውራት - ስም ማጥፋትም ከዚህ አይተናነስም፤ ሰውን፣ ቤተ ክርስቲያንን፣ ምዕመናኑን የሚያጠፋ ነገር ሲፈጸም ፈቅደን ትተናል፤ ስለ እውነትም አልተከራከርንምና ተለይተን አንታይም፡፡
- ያለሆነውን ሆኗል ብለን ማውራት - ስም ማጥፋትም ከሰይጣን ጋር መተባበር ነውና ስንተባበር አንገኝ፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፯

- ነህምያም ‹‹እኔም። አንተ ከልብህ ፈጥረኸዋል እንጂ እንደ ተናገርኸው ነገር ምንም የለም ብዬ ላክሁበት።›› ***ነህ 6፥8፡፡*** አለ፡፡ ያልከው ትክክል አይደለም አለው፡፡
- ቀጥሎም ‹‹እነርሱም ሁሉ ሥራው እንዳይፈጸም። እጃቸው ይደክማል ብለው ያስፈራሩን ዘንድ ወደዱ አሁንም፥ አምላክ ሆይ፥ እጄን አበርታ።›› ***ነህ 6፥9፡፡*** አለ፡፡
- ከነህምያ የምናገኘው ታላቁ ነገር እውነተኛ መሆኑ ነው፡፡ ‹‹ያስፈራሩን ዘንድ ወደዱ›› ማለት ምን ማለት ነው? ነህምያ ችግር የለውም ብሎ ነገሩን አላቀለለውም፡፡ ፈራሁ አለና ደካማ ነኝና አበርታኝ አለ፡፡ አሁን ከመሪዎች ደካማ ነኝ የሚል ይገኛል? እግዚአብሔር መንገዱን እንዲያመለክተው እንዲያበረታው የጠየቀ ብቸኛ መሪ ነው፡፡
- ምክንያቱም ደካማነቱን አምኖ እርዳታ የሚጠይቅ ከሆነ በሥራው የሚያግዙት ይኖራሉ፣ ሥራውም በአግባብ ይከናወንለታል፡፡ ሰዎች፣ ቤተ ክርስቲያን፣ እግዚአብሔር ረዳትነታቸው ያስፈልጉኛል ካልሆነ ብቻዬን አልችለውም የሚል እውነተኛ መሪ ነው፡፡
- ነህምያ በተባለበት ነገር ተጎድቷል፡፡ ዛሬም የፈለገትን ብለው ስሜን ቢ ያጠፉ ጉዳዬ አይደለም የምንል ሰዎች አለን፡፡ ይህም የማስመሰል መንፈሳዊነት ነው፤ ስም ማጥፋት የማይጎዳው የማያሳምመው የለምና፡፡ ታዲያ እነዚህ ስም በማጥፋት የተሰማሩም ከክርስቲያኖች ወገን አይቆጠሩም ከጠላት ዲያቢሎስ ጋር የሚሠሩ ናቸውና፡፡

3. ***ሃይማኖታዊ እንቅፋት አዘጋጁ፡፡*** ‹‹እኔም ወደ መሔጣብኤል ልጅ ወደ ድላያ ልጅ ወደ ሸማያ ቤት ገባሁ እርሱም ተዘግቶ ነበርና። በእግዚአብሔር ቤት በመቅደሱ ውስጥ እንገናኝ የመቅደሱንም ደጆች እንዝጋ እነርሱ መጥተው ይገድሉሃልና፥ በሌሊትም ይገድሉህ ዘንድ ይመጣሉና አለ።›› ***ነህ 6፡10፡፡*** ነህምያ ወደ አንድ ነቢይ ቤት ሄደ፡፡ ነቢዩም እነዚህ ሰዎች እየተከታተሉህ ስለሆነ የሚሻለው በቤተ መቅደስ ሄደን ብንደበቅ ነው አለው፡፡ በቤተ መቅደስ ብንደበቅ ከካህናት በቀር ወደዚያ ማንም ይገባ ዘንድ አይችልም፣ እዚያ መሆንህንም ማንም አያውቅም በዚያ ብትሆንም ትተርፋለህ አለው፡፡

- ነህምያ ከካህናት በቀር ለሌሎች ካልተፈቀደ እኔስ ስለምን በቤተ መቅደስ እደበቃለሁ? ቢል ነቢዩም እንዳይገድሉህ ነው አለ፡፡ ይህም ትልቅ ወጥመድ ነበር፡፡ እነርሱ አስወሩ ይህ ነቢይ ደግሞ ደፍሮ በቤተመቅደስ እንዲደበቅ ፈለገ፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፯

- የእግዚአብሔርን ሕግ በማፍረስ ሊያሳፍሩት ሲሉ ወጥመድ አዘጋጁለት፡፡
- ነህምያም ‹‹እኔም። እንደ እኔ ያለ ሰው የሸሽና፥ ነፍሱንስ ያድን ዘንድ ወደ መቅደስ የገባ ማን ነው? እኔስ አልገባም አልሁት።›› ***ነህ 6፥11።*** አለ፡፡ ይህ ታዲያ ሥርዓተ አልበኛ መሆኑ ነው፧ አልነበረም፡፡
- እኔ የፈራሁ እግዚአብሔር ለሥራው የመረጠኝ ሰው ነኝ፤ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ሕግ አፍርሼ በመቅደሱ እሸሽግ ዘንድ ይገባኛልን፧ አላደርገውም ወደ መቅደሱም አልገባም አለ፡፡
- ነህምያ ‹‹እግዚአብሔርም ልኮት እንዳልነበረ፥ በእኔ ላይ ግን ትንቢት እንደ ተናገረ፥ እነሆ፥ አወቅሁ ጦብያና ሰንባላጥም ገዝተውት ነበር። ይህንም ነገር አደርግና እበድል ዘንድ፥ በእኔም ላይ ክፉት እንዲናገሩና እንዲያላግጡ ያስፈራራኝ ዘንድ ተገዝቶ ነበር።›› ***ነህ 6፥12።*** አለ፡፡ ክርስቲያኖች ሆይ! ራሳችንን ለማዳን ስንል የእግዚአብሔርን ሕግ ስንጥስ እንዳንገኝ ይገባናል፡፡ ክርስቶስ አምላኬ እንደሆነ ባለ መከራከር ወይም ባለመናገር የገዛ ሕይወቴን ላተርፋት እችላለሁን፧ የተዘጋጀልንን መከራ የቀረበልንን ፈተና በጸጋ እንቀበል፤ እኛ እርሱ ካላዘነልን በቀር የገዛ ሥጋችንን በራሳችን ልናተርፈውና ልንታደገው አንችልምና፡፡
- በመቀጠልም ነህምያ ‹‹አምላኬ ሆይ፥ ስለዚህ ሥራቸው ጦብያንና ሰንባላጥን ያስፈራሩኝም ዘንድ የወደዱትን ነቢይቱን ኖዓድያን የቀሩትንም ነቢያት አስብ።›› ***ነህ 6፡፥13፡፡*** ብሎ ጸለየ፡፡
- ‹‹ቅጥሩም በኤሉል ወር በሀያ አምስተኛው ቀን በአምሳ ሁለት ቀን ውስጥ ተጨረሰ።›› ***ነህ 6፡፥15፡፡*** በማለት ቅጥሩን ሁሉ በ52 ቀናት ፈጸምሁ በማለት የእግዚአብሔርን ተአምር ነገረን፡፡ ሥራው የእግዚአብሔር ነውና፡፡
- ‹‹ጠላቶቻችንም ሁሉ ይህን በሰሙ ጊዜ በዙሪያችን የነበሩ አሕዛብ ሁሉ ፈሩ፥ በራሳቸውም አሳብ እጅግ ተዋረዱ፥ ይህም ሥራ በእግዚአብሔር እንደ ተደረገ አወቁ።›› ***ነህ 6፡፥16፡፡*** በማለት እግዚአብሔር ታላቅ ነው ብሎ ነገረን፡፡ ታላላቅ መሪዎች ክብርን ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሰጣሉ፤ ነህምያም ከነዚህ መሪዎች ታላቁ ነውና ክብርን ሁሉ ለእግዚአብሔር ሰጠ፡፡
- ነህምያ ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ ሥራው የእኔ አይደለም የእግዚአብሔር ነው ሲል ነበር፤ በርካታ ሰዎች ሥራውን የራሳቸው በማስመሰል በውጥረት ውስጥ ሆነው ጊዜ አጣን፣ አላልቅ አለን፣ ቆመ፣ … እንደሚሉት አላደረገም፡፡ ሥራው የእግዚአብሔር ነው በማለት ክብሩን ሁሉ ለርሱ ሰጠ እንጂ፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፲

- አገልግሎቱ የእኛ ሳይሆን የእግዚአብሔር ነው፡፡
- <<ጦብያም የኤራ ልጅ የሴኬንያ አማች ስለ ነበረ፥ ልጁም ይሆሐናን የቤራክያን ልጅ የሜሱላምን ሴት ልጅ ስላገባ፥ በይሁዳ ብዙ ሰዎች ከእርሱ ጋር ተማምለው ነበርና በዚያ ወራት ብዙ የይሁዳ አለቆች ወደ ጦብያ ደብዳቤዎች ይልኩ ነበር፥ የጦብያም ደብዳቤዎች ወደ እነርሱ ይመጡ ነበር። ደግሞም በፊቴ ስለ እርሱ መልካም ይናገሩ ነበር፥ ቃሌንም ያወሩለት ነበር ጦብያም ሊያስፈራራኝ ደብዳቤዎችን ይልክ ነበር።>> ***ነህ 6፥17.19***
- ከላይ እንደጠቀሰው ጦቢያ ከይሁዳ ለተመረጡት አለቆች ደብዳቤ እየላከ ነህምያን ለመቃወም ሌላ ዘዴ ቀየሰ፡፡ የይሁዳን አለቆችም ነህምያን የሚሰልሉና ከርሱም የሚያስታርቁት ሽማግሌዎች አድርጎ ይጠቀምባቸው ዘንድ ጣረ፡፡ አንዳንዶችም በነህምያ ፊት ስለ ጦብያ መልካምነት ለመመስከር ይሞክሩ የነበሩ ቢሆንም ነህምያ ግን አልተታለለም፡፡ እንዲህም ሆኖ ነህምያን የበለጠ ያስጨንቀው ዘንድ ደብዳቤዎችን ላከለት፡፡
- ይህም አንዱ አልሳካ ሲል ቤተ ክርስቲያንን ይከፋፍልና ግኑኝነታችንን ሁሉ ያበላሽ ዘንድ ሌሎች የውስጥ እንቅፋቶችን የሚያዘጋጀው የዲያቢሎስ መንገድ ነው፡፡ ነህምያ ከነዚህ ጋር ለመነጋገርም ሆነ ለመስማማት ፈቃደኛ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከዛሬው ትምህርታችን የምናጠናቸው ጥቅሶች፡
  - ‹‹አሁንም፥ አምላክ ሆይ፥ እጄን አበርታ።›› ***ነህ 6፡9፡፡***
  - ‹‹ይህም ሥራ በእግዚአብሔር እንደ ተደረገ አወቁ።›› ***ነህ 6፡16፡፡***
- ለማጠቃለል የመሪዎች ብዙ ጉልበታቸው በሆነው ባልሆነው በመታገል ይጠፋል፡፡ በነቀፋ፣ በእንቅፋት፣ ወዘተ ሥራው አልተቋረጠም፡፡ እስካሁን በተማርነው አይታችኋል፣ ሰዎች እንቅፋት ይፈጥራሉ፣ ያወራሉ፣ ይነቅፋሉ፣ ስም ያጠፋሉ፣… ተቃውሞው ከፍ ያለ ነው፡፡ ይህም የእግዚአብሔርን ሥራ ስንሰራ የተለመደ ነገር እንደሆነ እናስተውል፤ ይደረጋሉ እንጂ ሥራውን የማቆም አቅም የላቸውምና፡፡
- ነህምያ ከቤተ መንግሥት መጥቼ ከነዚህ ጋር ምን አታገለኝ አላለም፤ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ሥራውን ቀጠለ እንጂ፡፡
- ታላላቅ ሰዎች ስኬታማ የሆኑት ባለማቋረጥ ስለ ተጓዙ ነው፡፡ እኛ ታላቅ ነን ሳይሉ ፈጽመው ሥራቸውን ስላላቋረጡ ነው፡፡
- ***እኛስ ሥራችንን ፣ ዓላማችንን፣ ግባችንን፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ትተን ወደ ታች እንዴት እንወርዳለን?***
- የመሪ ሕይወት በነቀፋ፣ ተስፋ በሚያስቆርጥ አሠራር፣ በዛቻና በማስፈራሪያ የተከበበ ነው፡፡ ሌሎቹን ሳምንት እንማራለን፡፡

ይቆየን፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org